# ግንቦት ሰባት በሸገር ከደጋፊዎቹ ጋር ፊሽታ ያደርጋል (ግርማ ካሳ)

September 6, 2018

ወገኖች የግንቦት ሰባት አመራሮች የፊታችን ቅዳሜ ወይም እሁድ ሸገር በቦሌ ይገባሉ። አገር ቤት ያሉ የሰማያዊ፣ የቀድሞ አንድነት አባላትና በርካታ ወገኖች አቀባበል ያደርጉላቸዋል ተብሎ ይጠበቃል። አንዳንዶቹ እንደነገሩኝ አቀባበል የሚያደርጉት የወደፊቱን በማሰብ እንጂ ያለፈውን በማየት አይደለም።

ከታማኝ የማይተናነስ አቀባበል፣ ምን አልባትም ከዚያም የሚበል ከአዲስ አበባ እጠብቃለሁ። አንደኛ ግንቦት ሰባት ብዙ ደጋፊ አላቸው። ሁለተኛ ብዙ ገንዘብ ለአቀባበላቸው አፍሰዋል።

በሸገር ለግንቦት ሰባት የሚደረጉ ዝግጅቶች የሚያሳይ ፎቶ እየተለጠፈ ነው። አንዳንዶቹም "ግርማ ካሳ አሁን ምን ልትል ነው ? አታይም ሰው እንደሚደግፋቸው ? .." እያሉ እንደው የሕጻን ብሽሽቅ ነገር ይቃጣቸዋል።

አንደኛ ያፈሰሱትን ገንዘብ መጠን መርሳት የለብንም። ሁለተኛ ለነዚህ ወገኖች ግልጽ ላደርግላቸው የምፈለገው ነገር ቢኖር ድፍን አዲስ አበባ ለአንድ ግለሰብ ድጋፍ ቢሰጥ ፣ ሰው ደገፈ ብዬ በስሜት ተከትዮ የምሄድ ሰው አይደለሁም። ሶስተኛ የሸገር ሕዝብ ወደ ሰባት ሚሊዮን መሆኑን አንርሳ። ከዚያ ውስጥ አስር ሺህ ሰው ግንቦት ሰባትን ቢደገፍ ከ 0.01% በታች ነው። ስለዚህ ድርጅታችን ብዙ አቀባበል ተደረለት በሚል ጣራ ላይ ራሳችንን ባናወጣ ጥሩ ነው።

ከአዲስ አበባ ውጭ ምን አልባት፣ በወልቂጤ፣ አርባ ምንጭ ካልሆነ ብዙ ሰው የሚሰበሰቡበት ሁኔታ ይኖራል ብዬ አላስብም። በመሆኑም የግንቦት ሰባት አቀባበል ወሬ በቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል።

ከዚያ በሁዋላ ትልቅ ስራ ይጀመራል። ግንቦት ሰባቶች ምን አጀንዳ እንዳላቸው፣ የፖለቲካ ፕሮግራማቸው ምን እንደሚሆን የማወቅ እድል ይኖረናል። ለምሳሌ የዘር አወቃቀሩ እንዲፈርስና አዲስ ለአስተዳደር አመች፣ ከዘር ነጻ የሆነ አወቃቀር እንዲኖር በቁርጠኝነት ይነሳሉ ወይንስ ፣ የኦሮሞ ብሄረተኞችን ለማባባል፣ ለማስደሰትና ለስልጣን ሲሉ ኦነግና/ሕወሃት የሸነሸኑትን ይዘን እንቀጥል ይላሉ ? እነዚህንና ሌሎች መሰረታዊ በሆኑ የሕዝብ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚሉትን እንሰማለን። በዚህ ዙሪያ እንደ ሙሉነህ ኢዮ፡ኤል ያሉትን የተናገሩትን በማሰብ ግንቦት ሰባት ለኦሮሞ ብሄረተኞች ይሸጠናል የሚል ስጋት አለኝ።

የአንድነት ኃይሉም አሰላለፍ ወዴት አቅጣጫ እንደሆነ ፍንጭ እናገኛለን። "ግንቦት ሰባቶች ይምጡና፣ ከነርሱ ጋር ተነጋግረን፣ አጀንዳችንን ፕሮግራማችን የሚጣጣም ከሆነ፣ አብረን አንስራለን። ሁላችንም አንድ ጠንካራ ቢቻል እንደ ቅንጅት ያለ ካልተቻለም የቅንጅትን ያለ ስብስብ እንፈጥራለን " እያሉ ነው። እንደተመኙትና እንዳሰቡት ከሆነ እሰየው ነው።፡ በተለይም ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሆነው የሚመሰሩትን ድርጅት ግልጽነት፣

ተጠያቂነታ ዲሞክራሲያዊነት የተላበሰ ከሆነ በጣም ሃሪፍ ነው የሚሆነው። ብዙዎቻችንም ያለፈውም ረስተን አብረን ልንሰለፍ እንችላለን።

ግን ግንቦት ሰባቶች ሌላውን ጨፍልቀው እነርሱ የሚመሩት ስብስብ ካልሆነ ፣ እነርሱ ከሌሎች ጋር በእኩልነት የሚታዩበት ስብስብን ይደግፋሉ ብዬ አላስብም። ሚስጥራዊ ስለሆነ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ላይደገፉ ይችላሉ። በተለይም ዶ/ር ብርሃኑ እርሱ የበላይ ሆኖ የማይቆጣጠረዉና የማይመራው ስብስብን ይቀበላል ብዬ አላስብም። በዚህ በዚያም ብሎ፣ ሊፎካከሩት የሚችሉ ጠንካራ ታጋዮችን እንዲገለሉ በማድረግ (ስማቸውን በካድሪዎቹ በኩል እያስጠፋ) ውስጥ ውስጡን እነርሱ ላይ ዘመቻ በመከፈት፣ ከወዲሁም ከርሱ ጋር የሚፎካከር ማንም ሰው እንዳይኖር በማድረግ ፣ ቁንጮ ቦታዉን መያዙ አይቀሬ ነው የሚል ግምት ነው ያለኝ። እንዳልኩት ግምቴን ነው የጻፍኩት። ልሳሳት እችላለሁ። እንደውም ብሳሳት ደስ ነው የሚለኝ።

ለማንኛውም የምናየው ይሆናል። ለግንቦቴዎች እንግዲህ ለሚቀጥሊት ትቂት ቀናት ፊሽታ አድርጉ።